# በጳጳሣት ሹመት ዙሪያ አንዳንድ ነጥቦች –

**ይሄይስ አእምሮ**

June 20, 2016

ሰሞኑን ዘሃበሻ ድረገፅ በሰበር ዜናነት እንደዘገበችው በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ስድስት ኤጲስ ቆጶሣትን በሙሉ የጵጵስና ማዕረግ ሾሞ በስድስት የዓለም ግዛቶች በሃይማኖታዊ የኃላፊነት ቦታ መድቧል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይቺ ቅመም የሆነች ዘሃበሻ የምትባል ድረገፅ ዜናውን ተከታትላ በወቅቱ ስላደረሰችን ከፍተኛ ምሥጋና ይገባታል፡፡ ሌሎቹ ድረገፆችም እንዲሁ፡፡ ሁሉም የዘጠኝ ወር ልጆቻችን ናቸውና ምሥጋናየ ለሁሉም ነው፡፡ “ከጣት ጣት ይበልጣል”ን አለቦታው ልተርት አልፈልግም፡፡ ቢሆንም….አሉ ደግሞ አቁስሎች፡፡…

ይህ ሹመት በወያኔ ሤራ ምክንያት በካልቾ ተጠልዛ መሬት ላይ በመዘረር ነፍሷ አልወጣ ብሎ እያንቋረረች ለምትገኘው የሀገራችን ታሪካዊት ሃይማኖት ትንሣኤ የሚያበረክተው አወንታዊ ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ ማንሰራራት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያደረጉና በማድረግም ላይ የሚገኙ አባቶች፣ ወንድሞች፣ እናቶችና እህቶች ታላቅ ክርስቶሳዊ ምሥጋና ይገባቸዋል፡፡ ይህች የክርስቶስ መሠረት የሆነች ሃይማኖታችን በሁለት እግሯ እንድትቆምና የቀድሞውን ሕዝብን በአንድነትና በፍቅር የማሰባሰብ ሚናዋን እንድትጫወት እግዚአብሔር ያግዛት ዘንድ በበኩሌ እየጸለይኩ በሰሞኑ የሹመት አሰጣጥ ሂደት ላይ ከዜናዎቹ የታዘብኳቸውን አንዳንድ ነጥቦች ማንሳት ወደድኩ – እንዲያው አልሁ ለማለት ያህል እንጂ እስከዚህ ከባድ ሆነው አይደለም፡፡

ከአዲሱ ዜና ከዛሬው በመነሳት ስለስያሜያቸው ትንሽ ልበል፡፡ በአዲሱ ስያሜ አቡነ ቴዎፍሎስ የተባሉ አንድ አባት አሉ፡፡ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም በደርግ ፋሽሽት (ደርግን ከወያኔ ጋር ሳነጻጽረው ይህንን ቃል መጠቀም ከብዶብኝ መቸገሬን ተረዱልኝ) የተገደሉትን ሁለተኛውን የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክርስቲያን ፓትርያርክን ያስታውሰናል፡፡ ቀደም ሲል ለሌሎች አባቶች የተሰጡ ሌሎች ተመሳሳይ ስያሜዎችም አሉ – እንደ አቡነ ጴጥሮስ ዓይነት ለምሣሌ፡፡

እኔ እምለው ታዲያ አዲሱን አባት በሌጣው “አቡነ ቴዎፍሎስ” ብለን ከምንጠራ “አቡነ ቴዎፍሎስ ዳግማዊ(2ኛ)” ብለን ብንጠራ አይሻልም ነበር ወይ? ነው፡፡ አንድ ነገር ከታመነበት ምን ጊዜም ማስተካከል ይቻላልና የሚመለከታቸው ወገኖች ቢያስቡበት መልካም ይመስለኛል፡፡ ምክንያት አለኝ – ምክንያቴ ደግሞ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ተራ ስሞችን ማንም ቢጠቀምባቸው ችግር የለውም፡፡ ለምሣሌ በመቶዎች የሚቆጠሩ “ይሄይስ” የሚባሉ ስሞች በኢትዮጵያ ውስጥና ውጪ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ያ ምንም ማለት አይደለም፡፡ የማዕረግና የሹመት ስሞች ግን አንዱን ከሌላው እንዳያምታቱ ተጨማሪ መግለጫ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህም ነው ለምሣሌ ዳግማዊ ቴዎድሮስ፣ ዳግማዊ ምንሊክ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሤ፣ አፄ ዮሐንስ አራተኛ፣ ሉዊስ 16ኛ፣ ጆን ፖል ሁለተኛ፣ ቤኔዲክት 16ኛ… እየተባለ የሚጠራው፡፡ አንድ ሰው ተነስቶ “አቡነ ቴዎፍሎስ እጅግ የተከበሩና በሕዝብ የተፈቀሩ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ፡፡ በስማቸውም አንድ የበጎ አድራት አቋቁመው ደሞዛቸውን እንዳለ ወደዚያ ድርጅት ነበር ፈሰስ የሚያደርጉት፡፡…” ብሎ ቢጽፍ ስለየትኛው ቴዎፍሎስ እየተናገረ እንደሆነ ተጨማሪ መግለጫ ወይ ማብራሪያ በግርጌ ማስታወሻ መስጠት ይጠበቅበታል፤ አለበለዚያ አንባቢን ያደነጋግራል፡፡ ስለዚህ ሌላ አሳሳች መጠሪያ ያለባቸው አዲሶቹ ተሹዋሚዎች በስማቸው ላይ ቁጥር ቢደረብ ጥሩ ነው እላለሁ – ተለይተው እንዲታወቁ፡፡ ይህ ደግሞ የአእምሮ ዕድገት ምልክት እንጂ ሌላ ፍቺ ሊኖረው አይችልም፡፡

በበቀደሙ ዜና ደግሞ በ 10 ዓመታቸውና በ 12 ዓመታቸው የዲቁና ማዕረግ የተሰጣቸው የቀድሞ ሕጻነት የአሁን አባቶች

እንደነበሩ ተገልጾኣል፡፡ የአሥር ዓመት ልጅ የዲቁና ማዕረግ ይሰጠዋል? ከሆነ ጥሩ፡፡ ካልሆነ ግን መረጃው በውል መፈተሽ ነበረበት ወይም አለበት፡፡ የዕድሜ ነገር አወዛጋቢና አስተዛዛቢም ስለሆነ ይህ ዓይነቱ ነገር ቢያንስ ለወደፊቱ ይታሰብበት፡፡

ከዚህ በተያያዘ አንድ አባት በ 17 ዓመት ዕድሜያቸው መንኩሰው ለቅስና ክህነት እንደበቁ ተዘግቧል፡፡ በዚህ እኔም በጣም ግር ብሎኛል፡፡ ባለኝ ግርድፍ ሃይማኖታዊ ዕውቀት አንድ ሰው ቄስ ለመሆን ቢያንስ የ 30 ዓመት ጎልማሣ ሊሆን ይጠበቅበታል – እንኳን ምንኩስና፡፡ ምንኩስና ደግሞ ብዙ የጥሞናና የእውነተኛ ጥሪ ማስተማመኛ ጊዜ ያስፈልገዋል፡፡ “ነገሩ ካንገት ነው ወይንስ ካንጀት” – “ጥሪው መለኮታዊ ነው ወይንስ ሰይጣናዊ” ተብሎ መጣራት አለበት፡፡ “በ 17 ዓመት ይመነኮሳል፣ በ 17 ዓመት የቅስና ክህነት ይሰጣል” ብዬ ደግሞ አላምንም – ሆኖም ከሆነ አንድ ቦታ ላይ ስህተት መኖር አለበት፡፡ ይህም መረጃ ይጣራና ማስተካከያ ወይም ማስተባበያ ይሰጥበት – አንድ ዜጋ ጠየቀ -እኔ፡፡ የ 17 ዓመት ታዳጊ ምን ያውቅና፣ ምንስ የሕይወት ተሞክሮ አለውና ነው ምንኩስና ላይ የሚደረብ ቅስና የሚሰጠው? አስረዱኝ፡፡

አንድ ዲያቆን ከደቆነ በኋላ በርከት ላለ ጊዜ በዚህ ማዕረግ ያገለግላል፡፡ ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት 30 ዓመት ሲሞላውና አስፈላጊውን ዕውቀትና ትምህርት አሟልቶ ሲገኝ የቅስና ማዕረግ ይጠይቃል፡፡ ይሄኔ አንድም ማግባቱ አንድም መመንኮሱ ይረጋገጥና ተፈትኖ ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ ማዕረገ ክህነቱ ይሰጠዋል፡፡ የ 17 ዓመት ልጅ እንግዲህ አንድም ለጋብቻ አንድም ለምንኩስና አልደረሰምና ጥያቄ ያስነሳል፡፡ (የቃል ፈተናው ላይ ሦስቱ ሥላሦችን አስረዳ የተባለ የቅስና ማዕረግ ለመቀበል ያመለከተ አንድ አንጋፋ ዲያቆን የሥላሤ ጽላቶች የሚገኙባቸውን ሦስት ደብሮች እንደጠቀሰና ፈታኞቹን በሣቅ እንደገደላቸው ሰምቻለሁ – “ከመጠምጠም መማር ይቅደም” የተባለውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መሰለኝ፡፡)

የአራቱ አባቶች የትውልድ ቦታ በደምሳሳው “ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ዓመተ ምሕረት ተወለዱ” ይልና ሁለቱ ግን ከአራቱ በተለዬ የተወለዱበት ሥፍራ አንዱ በትክክል ሌላው “ሰሜን” በሚል በገደምዳሜ ተጠቅሷል፡፡ የአራቱ በጣም ተስማምቶኛል – ካህን ሀገር ስለሌለው፡፡ የሌሎቹ የሁለቱ ግን እንደሌሎቹ እንዳራቱ መሆን ነበረበት – ተለጣጣቂነቱ እንዳይፋረስ (consistence እንዲኖረው)፡፡ በቃ፡፡ አንዳንድ ነጥቦች አልኩ – እነሱንም እንደነገሩ ጨረስኩ፡፡

***http://www.ethiopanorama.com***